## የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ፐብሊክ ሰርቪስ ኮሚሽን

### ለዲስትሪክቱ ሀይል ማቅረብ

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ፐብሊክ ሰርቪስ ኮሚሽን ለከተማዋ አገልግሎት የሚያቀርቡ የኤሌክትሪክ፣ የተፈጥሮ ጋዝ እና የስልክ ኩባንያዎችን የሚቆጣጠር የዲስትሪክቱ መንግስታዊ መ/ቤት ተደርጎ በኮንግረሱ የተቋቋመው በ1913 ነበር።

ጤናማ የፋይናንስ ስርዓት ያላቸው የመሰረታዊ አገልግሎት አቅራቢዎች በዲስትሪክቱ ውስጥ ለሚገኙ መኖሪያ ቤቶች፣ ድርጅቶች እና መንግስታዊ መ/ቤቶች/ደንበኞች ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አስተማማኝ እና የጥራት ደረጃውን ያሟላ መሰረታዊ አገልግሎት እንደሚያቀርቡ በማረጋገጥ ኮሚሽኑ የሕዝብን ጥቅም ያስጠብቃል፡ ፡

ዲሲ.ፒ.ኤስ.ሲ የሚመራው በአንድ ሊቀመንበር እና በሁለት ኮሚሽነሮች ሲሆን፤ የዲሲ ምክር ቤት በሚሰጠው ምክር እና ፈቃድ መሰረት ሁሉም ለአራት አመታት የአገልግሎት ጊዜ በከንቲባው የሚሰየሙ ናቸው። የመ/ቤቱ አመታዊ በጀት የሚገኘው ከግብር ከፋዮች ሳይሆን ከሚቆጣጠራቸው ኩባንያዎች ከሚፈጸም ክፍያ ነው።

### ንጹህ ሐይል

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ዘላቂነትን እና አካባቢያዊ ጥበቃን በተመለከተ በሃገር ደረጃ የመሪነቱን ስፍራ የጨበጠ ሲሆን፤ በሃገሪቱ ውስጥ ከሚገኙ ማንኛውም ከተሞች ካስቀመጧቸው የታዳሽ ሀይል መስፈርቶች ውስጥ ጥብቅ መስፈርት ካላቸው መካከል አንደኛው ነው። የዲስትሪክቱ አመራር የአለም የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸውን ተጽእኖዎች ለመዋጋት እና ለወደፊቱ ንጹህ ሃይልን እውን ለማድረግ በቁርጠኝነት ይሰራል።

እንደ አካባቢያዊ የመሰረታዊ አገልግሎት ተቆጣጣሪ አካል የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ፐብሊክ ሰርቪስ ኮሚሽን እነዚህን ግቦች ለማሳካት የሚጫወተው አስፈላጊ እና ወሳኝ የሆነ ሚና አለው።

ፈጠራን፣ ደህንነትን፣ እኩልነትን እና ተመጣጣኝ ዋጋን የሚያበረታታ የሐይል አቅርቦት ስርዓት በዲስትሪክቱ ውስጥ ለመፍጠር በሚችል አካታች የግሪድ ማዘመን ፕሮጀክት በፓወርፓዝ ዲሲ (የረጅም ጊዜ ብሉ ፕሪንት)

አማካኝነት ዲሲ.ፒ.ኤስ.ሲ ለወደፊት የሚኖረውን የቁጥጥር መንገድ ጥርጊያ እያበጀ ነው። ፓወርፓዝ ዲሲ የኮሚሽኑን ስራ ይመራል እናም ኤጀንሲው በሁሉም ውሳኔዎቹ የዲስትሪክቱን የንፁህ ኢነርጂ ፖሊሲ ግቦችን እንደሚያጤነው ያረጋግጣል።

ከዚህም በተጨማሪ ፓወርፓዝ ዲሲ የከተማውን የሐይል አቅርቦት ስርዓት ዘመናዊ የሚያደርጉ እና የዲስትሪክቱን የንጹህ ሐይል እና የአየር ንብረት ግቦች የሚያሳኩ ተከታታይ የፈጠራ ፓይለት ፕሮጀክቶችን ይመራል። እነዚህ ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው ፕሮጀክቶች አብዛኛውን ጊዜ በሐገሪቱ ውስጥ በአይነታቸው የመጀመሪያ ከሆኑት መካከል የሚገኙ ሲሆን፤ የታዳሽ ሐይል መሰረተ ልማትን ለማሻሻል፣ የላቀ ለማድረግ እና ከፍ ለማድረግ ያግዛሉ። ከሌላ የመሰረታዊ አገልግሎት የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው የአረንጓዴ ማሻሻያዎች እና ቴክኖሎጂያዊ ፈጠራዎች በተጨማሪ፤ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አስተማማኝ እና የማይበገር መሰረተ ልማት እንዲኖር ከማስቻል ጎን ለጎን ፓይለት ፕሮጀክቶቹ የዲስትሪክቱን የንፁህ ሐይል ግቦች ይደግፋሉ።

### የታዳሽ ሐይል ፖርትፎሊዮ መደበኛ መርሃ ግብር (አር.ፒ.ኤስ)

ዲሲፒ.ኤስ.ሲ ያወጣውን ሕግ ተከትሎ፤ በዲስትሪክቱ ውስጥ የሚገኙ የኤሌክትሪክ ሐይል አቅራቢዎች እየጨመረ በሚሄድ መቶኛ የኤሌክትሪክ ሐይልን ከታዳሽ ምንጮች ማቅረብ ይኖርባቸዋል። የአርፒኤስ ፕሮግራም በዲስትሪክቱ ውስጥ ከታዳሽ ምንጮች ለሚገኝ የኤሌክትሪክ ሐይል ገበያ የሚፈጥር ሲሆን የታዳሽ ግብዓቶች መኖርን የሚያብራራ ይሆናል።

### የንጹህ ሐይል ጉባኤ

በዲሲፒኤስሲ የሚዘጋጀው አመታዊው የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የንጹህ ሐይል ጉባኤ የዲስትሪክቱን ጥብቅ የሆኑ የአየር ንብረት ፖሊሲ ግቦቹን ለማሳካት፣ አዳዲስ መስፈርቶችን ለማስቀመጥ እና የዲስትሪክቱ የንጹህ ሐይል ሽግግር ፍትሃዊ፣ ውድ ያልሆነ እና የማይበገር የአየር ንብረት የሚፈጥር መሆኑን ለማረጋገጥ ተፈላጊ ሁኔታዎችን የሚያስቀምጡ ኤክስፐርቶችን/ባለሙያዎችን መሪዎችን እና ሌላ ፕሮፌሽናሎችን በአንድ ላይ የሚያሰባስብ ነው።

### የአቅራቢ እና የግብረ ሐይል ስብጥር

ዲሲ.ፒ.ኤስ.ሲ የዲስትሪክቱን የንጹህ ሐይል ግቦች ወደፊት የሚያራምዱ የተለያዩ ግብረ ሐይሎችን እና የአቅርቦት ሰንሰለቶችን በማጎልበት ድጋፍ ያደርጋል። በመሰረታዊ አገልግሎት ዘርፍ የሚደረጉ ውሎች እና የሥራ ቅጥርን በተመለከተ ስብጥር፣ እኩልነት እና ማካተት እንዲኖር የሚያስችሉ አዳዲስ አስተያየቶች እና ጥሩ ተሞክሮዎች የሚመነጩት ከመንግስት መሰረታዊ አገልግሎት አቅራቢዎች፣ ስራ ተቋራጮች፣ የንግድ ማሕበራት፣ አካባቢያዊ ኮሌጆች እና ዩኒቨርስቲዎች እንዲሁም ከሌላ የኢንዱስትሪው ባለድርሻ አካላት የተውጣጡ ተወካዮችን ከሚያካትተው ገለልተኛ ከሆነው የዲሲ.ፒ.ኤስ.ሲ የመሰረታዊ አገልግሎት አቅራቢዎች እና ግብረ ሐይል ስብጥር አድቫይዘሪ ምክር ቤት ነው።

## ተደራሽነት እና የሸማች አገልግሎቶች

ከቁጥጥር ተግባራቱ በተጨማሪ ዲሲ.ፒ.ኤስ.ሲ የመሰረታዊ አገልግሎት ማጭበርበሮችን፣ ወደ ሶስተኛ ወገን የሐይል አቅራቢዎች መዞርን፣ የመሰረታዊ አገልግሎት ዋጋ ቅናሽ ፕሮግራሞችን በተመለከተ ለሕዝቡ ትምህርት እና መረጃ የሚሰጥ ከመሆኑ በተጨማሪ ሌላ የሐይል እና የገንዘብ ቁጠባ ምክሮችን ይሰጣል። የምክክር መድረክ እንዲኖር ለማስቻል እና የነዋሪዎቹን ስጋት ለመረዳት ኮሚሽኑ በዲስትሪክቱ ውስጥ ከሚገኙ ነዋሪዎች እና የማሕበረሰብ ቡድኖች ጋር አብሮ ይሰራል።

## መሰረታዊ አገልግሎትዎን በተመለከተ እርዳታ ይፈልጋሉን?

ዲሲ.ፒ.ኤስ.ሲ በሸማቾች እና በመሰረታዊ አገልግሎት አቅራቢዎች መካከል ለሚፈጠሩ ያለመግባባቶች መፍትሄ ለመስጠት ድጋፍ ያደርጋል። በ dcpsc.org/help አማካኝነት ከ ዲሲ.ፒ.ኤስ.ሲ ጋር ግንኙነት ይፍጠሩ ወይም በ(202) 626-5120 ይደውሉ።